# ኤርትራና ኢትዮጵያ-- ነገን በተመለከተ

ጀምበር ማንተስኖት
(የፖለቲካ ታዛቢ)

ከአንድ አንጋፋ የፖለቲካ ድርጅት አለአግባብ ወጥተው አንጃ መሰረቱ የተባሉት አንድ አዛውንት ባለፈው ሰሞን ለአሜሪካ ድምፅ ራዲዮ በሰጡት ቃለ መጠይቅ ተቀናቃኜ ያሏቸውን ግለሰብ ለማሳጣት ሲሞክሩ ወደ ኤርትራ እየተመላለሱ ከአቶ ኢሳያስ ጋር ይገናኛሉ ብለው በመክሰስ ተናግረዋል፡፡ ይህም የኢትዮጵያን ህልውና ለአደጋ የሚያጋልጥ ድርጊት ነው ለማለት ም ሞክረዋል፡፡ እውን ከአቶ ኢሳይያሰ መገናኘት ኢትዮጵያን መጉዳት ነውን? አዛውንቱ ራሳቸ ውን ማሞ ቂሎ አደረጉ ሲል የኢትዮጵያ ሬቪው ድረ ገፅ የተቻቸው ሲሆን ከእሳቸው ግራ የተጋ ባና አለስፈላጊ ንግግርና ክስ ባሻገር ግን ፀረ ወያኔ ኢትዮጵያውያን ኤርትራን በተመለከተ ምን አቅዋም ሊኖራቸው ይገባል የሚለው አነጋጋሪ ጉዳይ በመሆኑና አቶ ኒዓሚንና ሻለቃ ዳዊት ወልደ ጊዮርጊስም በጉዳዩ ስለተቹ የበኩሌን በአጭሩ ማቅረብ እፈልጋለሁ፡፡

ኤርትራን በተመለከተ ዛሬም ቢሆን አንድ ወጥ አመለካከት የለም፡፡ ዳር ድንበራችን ቀይ ባሕር ነው፤ ሻዕቢያም ደመኛ ጠላታችን ነው የሚሉ አሉ፡፡ ኤርትራ ነፃ ሆናለችና አብቅቶለታል ጉዳዩ ግን (ሀ) ከሻዕቢያ ሆነ ከነፃ ኤርትራ ምንም ግንኙነት አያስፈልግም (ለ) ከሻዕቢያ ወይም የኤ.ርትራ መንግሥት ጋር የጎረቤት ግንኙነት ያስፈልገናል የሚሉ አሉ፡፡ የትግሉን ጉዳይ በተመ ለከተ ሻዕቢያ አጋራችን ነው ሊሆን ይገባል የሚሉ ሲኖሩ ( ብለውም በኤርትራ መሬት ጦር የመሰረቱ አሉ)፤ በሻዕቢያ እርዳታ ለኢትዮጵያ የሚጠቅም ትግል አካሂዳለሁ ማለት ዘበት ነው የሚሉም በርካታ ናቸው፡፡ ይህ የተለያየ አቅዋም በመሰረቱ ችግር መፍጠሩ የሚካድ አይደለም፡፡ አቶ ኒዓሚን በፅሁፋቸው ያስቀመጡት ዋና ሀሳብ ከኤርትራ ወይም ሻዕቢያ ጋር ግንኙነትን ማድረግ አለብን የሚል ነው፡፡ ይህን ሀሳብ ወይም አቅዋም ሻለቃ ዳዊት ይጋራሉ፡፡ ሻለቃ ዳዊት ብዙ የወታደርነት ዓመታትን በኤርትራ ያጠፉ በመሆናቸውና ኋላም በደርግ ጊዜ በዚያው በአስተዳዳሪነትም የሰሩ ናቸውና ዕይታቸውና ትንተናቸው በሚገባ ከቀረበ ሚዛን አለው፡፡ ከሻለቃ ው ዝርዝር ፅሁፍ በቅድሚያ በበኩሌ ጫና ሰጥቼ ላቀርብ የምፈልገው ምንም እንኳን ያን የፈረደ በትን ትውልድ ወረፍ ከማድረግ መቆጠቡ ቢሳናቸውም የኤርትራን ቀውስ በዋና ደረጃ ያባባሱት ያለፉት አገዛዞች ናቸው ያሉትን ነው፡፡ ብዙ አላዋቂዎች በተለይም በደርጋዊና ወያኔያዊ ድረ ገፆችና ጥራዝ ነጠቅ ፅሁፎች አማካኝነት የኤርትራን ችግር ኢሕአፓ የተባለ ድርጅት የፈጠረው አስመስለው ማቅረብ ይወዳሉና ሻለቃ ዳዊት የችግሩን መንስዔና ለምንም ሊባባስ ቻለ በሚለው ደረጃ ያሰፈሩት ሀቅ ትምህርታዊ ነው፡፡ የኤርትራ ግንባር ጃብሀ ታላቁ ጀግና የሚለው ኢድሪስ አዋቴ ተራ ሽፍታ እንደነበረ ከሻለቃው በፊት የጀብሀ አባል የነበሩትና በኋላም በደርግ ስር ኤር ትራ ውስጥ ከሻለቃው ጋር የሰሩት አቶ አማኑዔል ገብረ ኢየሱስ በሰፊው አቅርበውታል፡፡ በዚህ በዚያም ግን የኤርትራ ችግር በአፄ ኃይለ ሥላሴ ስርዓትና በደርግ ስህተትና እርምጃዎች የተባባ ሰ መሆኑን ሻለቃው ያቀረቡት ሀቅ ጠቃሚ ነው፡፡

ከዚህ ባሻገር ግን ሻለቃ ዳዊት ካደረጉት ትንተና ስነሳ ከነገው አንፃር የዋህነትን ላለመድገም በሚ ል አንዳንድ ነጥቦችን ማንሳት እገደዳለሁ:: በተራ ተራ ማቅረቡ ነገሮችን ግልፅ ያደርጋል በሚል ም አንድ ሁለቱ እነሆ፤

1. ሻለቃ ዳዊት በመንግሥቱ ላይ በተካሄደው መፈንቅለ መንግስት ሙከራ ከኤርትራ በኩልም ቢሆን ተሳታፊ ነበሩ:: ይህ መፈንቅል ድገሞ በአሜሪካ የተዘጋጀ መሆኑ የሚታወቅ ነው:: ከዚህ መፈንቅል በተያያዘም ሆነ ከዘላቂ የአሜሪካ ውጥን አንፃር በነአቶ ደረጀ ዴሬሳና ኮሞዶር ጣሰው ይመራ የነበረው ኢሕዴአ /ኢፒዲኤ/ ም ቦታ ያገኘ ዘንድ ሻዕቢያ እስረኛ ወታደሮች ሊለግሰው፤ በኢዲኅና ሱዳን አማካኝነት ደግሞ ኢሕአፓ ተጠቅቶ ከሜዳ ቦታ እንዲለቅ እንዲደረግ ሴራዎች በስራ ሊውሉ ተሞክረው ነበር:: ( ከዚህ በተያያዘ የኮሞደር ጣሰው የሕይወት ታሪክ መፅሀፍ ብዙ መረጃን ያቀርባል):: በዚህ መልክ በአሜሪካና ከአሜሪካ በተያያዙ መኮንኖችና የቀድሞ ሚኒስቴ ሮች ብዙ ሴራ ተካሂዷል:: መፈንቅሉ ከመደረጉ በፊት እንዴት ታወቀ? ብዙ ሌሎችም ጥያቄዎ ች እስከዛሬ ግልፅ መልስ አላገኙም:: ሻለቃ ዳዊትና የደርግ መኮንኖች ስለ ሻዕቢያ የነበራቸው ግንዛቤ ደካማ ስለነበር ( በነ ሻለቃ ዮሴፍ ዳግም በኤኤፍዲ ጊዜ እንደታየው) ኢሳያስ አፈወርቂ የተኩስ አቁም አደርጋለሁ፤ በጋራ የሽግግር ሂደት እሳተፋለሁ ሲላቸው አምነውት ነበር:: ተቋቁ ሞ የነበረው የመኮንኖች ድርጅትም ለሻዕቢያ መሳሪያ እንዲሆን እንጂ ለኢትዮጵያ እንዲያገለግል ቢያንስ በሻዕቢያ ታስቦ አልነበረም ብንል እውነት ነው:: ይህ ሻዕቢያ ወይም መሪው የሚለውን በጭፍን የማመን ትልቅ ስህተት መሆኑን በመካድ ዛሬም ለመከራከር መሞከር ተገቢ አይደለም:: ኢሳያስ አፈወርቂና ጓደኞቹ ወደ ትግል ሜዳ የገቡት ብሔርተኞች ስለነበሩና ይህም አቅዋማቸው ኢትዮጵያን ሳይሆን ኤርትራን የተመለከተ--ያፈቀረ ስለነበር ነው:: ሻዕቢያ ተራማጅ ድርጅት ነው/ሊሆን ይችላል ብለው ያመኑና ከኢትዮጵያ እንቅስቃሴም ጋር አብሮ በጋራ ለኢትዮጵያ ሊታገል ይችላል ብለው የገመቱ ግምታቸው ስህተት ከመሆኑ አልፎ በሕይወታቸውም ዋጋ ከፍለዋል:: ሻዕቢያ ኤርትራ የኢትዮጵያ ቅኝ ግዛት ናት ብሎ በማመኑና ኢሕአፓም ይህን ባለመቀበሉ መጣላታቸውና መጋጨታቸው ተደጋግሞ የተገለፀ ና አሌ ያልተባለ ጉዳይ ነው:: በአጭሩ ሻዕቢያ ለኤርትራ ነፃነት የታገለና ሲታገልም የቆየ ድርጅት ነው:: በመሆኑም ደርግን የሚያዳክምና በተለይም ሠራዊቱን የሚጎዳ መፈንቅል ሙከራን መደገፉ የሚጠበቅና የብልጥ ስራም ነው::መፈንቅሉ ሲከሽፍ (ቀደም ብሎ የተጋለጠም ነበርና) መንግሥቱ ጀኔራሎችን አርዶ የጦሩን ሞራል ይበልጥ አድቅቆ ለሻዕቢያና ወያኔ የተመቻቸ ሁኔታ ፈጥሯል:: ( መፈንቅሉን በመ ደገፍ የአሜሪካ ሚና ገና ከመጀመሪያው ይህ ነበር የሚሉም አንዳሉ ከዚህ መጥቀስ ያስፈልጋል): : የኢትዮጵያ ጦር በተዳከመበት ሁኔታ ግን መፈንቅሉ ቢሳካም ኖሮ ኢሳያስ እነ ሻለቃ ዳዊትን ወግዱ ይላቸው እንደነበር መገመት አያዳግትም:: የዚህን ትምህርታዊነት ለዛሬ የምንመለስበት ጉዳይ ይሆናል::

2. ከላይ ከዘረዘርነው ጋር በተያያዘ መልኩ ሌላ በሻለቃ ዳዊት የቀረበው የዋህ ድምዳሜ ደግሞ ኢሳያስ አፈወርቂ ይህንን ብሄርተኛ አቀዋሙን ትቶ ኢትዮጵያዊና የኢትዮጵያም መሪ ሊሆን ይችላል የሚል ነው:: ኢትዮጵያን ከዚህ ዓይነት መቅሰፍት ፈጣሪዋ ይጠብቃትና ኢሳያስን ከኤርትራ ብሄርተኛነቱ ነጥሎ ማየት ሌላ የዋህነት ነው:: የኢትዮጵያ ፕሬዚዳንት ሁን ብለነው ነበር፤ ነፃ እንውጣና ስለ አንድነት እናወራለን ብሎ ነበር፤ ወይም በቅርቡ በእነ አቶ ኤልያስ ክፍሌ በቀረበው ቃለ መጠየቅ ላይ ሊንፃረቅ እንደከጀለው ኢሳያስ አፈወርቂ ለአንድነት የቆመ ነው ብሎ ለድምዳሜ የሚገፋ ምንም ተጨባጭ ሀቅ የለም:: በትግሉ ዘመን ሻዕቢያ የኤርትራ ብሄርተኝነት ነፀብራቅ ሆኖ ከመቆየቱ ሌላ ለኢትዮጵያ የሚታገሉትን ትምክህተኛ ብሎ ፈርጆ ከወያኔ ጎን መቆሙ የሚታወቅ ነው:: በዘመነ ደርግ የነ ሌንጮ ለታን እጅ ይዞ ኦነግ በሉ ብሎ የቃኘ ሻዕቢያ ነው:: ወያኔን በጦርም ያጠናከረና አዲስ አበባም ድረስ ያጀበ ሻዕቢያ ነው:: አዲስ አባባ ከመድረሳቸው በፊትም በለንደኑ ኮንፈረንስ ኢዴኃቅ መሳተፍ የለበትም ብሎ ሻዕቢያም መከራከሩን ሄርማን ኮኅንም አምኗል:: ወያኔ ለሥልጣን ከበቃ በኋላም ሻዕቢያ ለኢትዮጵያ የመቶ ዓመት የቤት ስራ ሰጥተናል ብሎ መፎከር ብቻ ሳይሆን ከወያኔ ጋር አብሮ ኢትዮጵያ በሚጎዳና የኢትዮጵያውያንን ልብ ባቆሰለ መንገድ ሲንቀሳቀስ መቆየቱን፤ ኢትዮጵያውያንን በገፍና በግፍ ማባረሩን ወዘተ ሊረሳ የሚችል ዜጋ አለ ብሎ መገመት ያዳግታል:: ማለትም ጊዜ ባመቸው ሁሉ ሻዕቢያ ማለትም ኢሳያስ ከኢትዮጵያ ጠላት ከወያኔ ጎን ቆሞ ነበር:: ስለዚህም አዲስ ታሪክ ሊተርክ ኢሳያስ ሲሞክር ለማጀብ መነሳቱ ዳግም ተላላነትና አልፎም ሀገርን መጉዳት ይሆናል:: በእርግጥ ዘላለማዊ ጠላትና ወዳጅ የለም በሚል ሌላ መንገድን መሻት ያለና ሊታይም የሚገባው መንገድ ቢሆንም መሞኘት ግን በአሁኑ ጊዜ በሀገር ላይ መቀለድ ነው::

3. ጄኔራል ቁምላቸው ስለ መፈንቅሉና የባዕዳን ሚና ለታሪክ ገለፃ ሳይሰጡ እንዳለፉት ሁሉ ሻለቃ ዳዊትም ስለዚያን ጊዜ ውስብስብ ግልፅልፅ አድርገው ባይነግሩንም መፈንቅሉ ቢሳካ ኖሮ በደፈናው የተለየ ሁኔታ ሊፈጠር ይችል ነበር ለሚሉት ምስክር ጥሩ አንላቸውም:: ይህ ልዩ ሁኔታ ግን የኢሳያስን በኢትዮጵያ የሽግግር ሂደት መሳተፍን የሚያስከትል ከነበረ ለምን ታዲያ በሰኔው 93 ጉባዔ ይህን ምርጫ እነ ኢሳያሰ አልወሰዱም ብሎ መጠየቁ ትክክል ነው:: ምንም እንኳን የአቶ ኢሳያስ የግል ሥልጣን የሚታወቅ ቢሆንም የአንድ ድርጅትና ተከታዮቹ ብሄራዊ ስሜት አንድ ቀን ጠዋት እንደ ቧምቧ ሊዘጋ የሚችል አይደለም:: ለሰላሳ ዓመት አደየ ኤርትራ ብለው ታግለው ሰኔ 83 ኢሳያስ ኢትዮጵያዊ ሆነናል ቢላቸው ይቀበሉታል ብሎ መገመትም ስህተት ነው::እሱ ራሱ ካለመፈለጉ ሌላ ተቀናቃኞቹም በከሀዲነት ሊከሱና ሊነጥሉት እንደሚችሉ መገንዘብ የሚያቅተው ሰው አይደለም:: ከኢትዮጵያ ጋር በፌዴሬሽን ወይም ኮንፌዴሬሽን ለመኖ ር ፈልገንም ነበር የሚል ከነበረ ይህ የፌዴሬሽን አማራጭ ከ 1983 በፊት ሲቀርብ አቅራቢዎቹን በትምክህተኛነት ለምን ከሰሰ? ሚቹየ ሻዕቢያ መሪ ኦስማን ሳሌህ ሳቤ ከደርግ ጋር በአሰብ ላይ እንደራደር በማለቱ ከሀዲ ተብሎ በአቶ ኢሳያስ ጥምብ ርኩሱ ወጣ ተብሎ የተፃፈውስ የሀሰት ወሬ ነው? ብዙመሰረታዊና ሊታለፉ የማይገባቸው ጥያቄዎች አሉ:: ለነዚህ የነሻለቃ መልስ

ደከማ ወይም በተስፋና ምኞት እንለፈው ዓይነት ነው:: ወያኔ ፀረ ኢትዮጵያ ነው የሚለውን ባለማመንና ከደርግ አይብስምን ምኞት በመያዝ ለወያኔ ሰለባ መሆናችንን ማስታወስ ያስፈልጋል ::

4. ዛሬ በጭፍኑ ሻዕቢያን አምናችሁ በእሱ ስር ለመሰለፍ ወይም ለመረዳት ለመታገዝ ተነሱ ብለው ሰበካ የጀመሩት ክፍሎች እውነትም የሚሉትን በሚገባ አስበውበት ይሆን ወይስ ሌላ ማጠየቂያ አላቸውን ብሎ መታዘብ ተገቢ ነው:: ሻለቃ ዳዊት ብዙ ተመክሮ የገበዩ ቢሆኑም በተወሰነ ወቅት ደግሞ የደርግ ዕቅድ አስፈፃሚ የነበሩ ናቸውና ይህ የነበረውና ያለውን ተፅዕኖም በቀላሉ ልናየው አንችልም:: በመፍንቅሉ በመካፈል ለጦሩ መዳከም አስተዋፅዖ አድርገው ለሻዕቢያ አልጠቀሙምን? ከፅሁፋቸው ስነሳ ደግሞ ኢሳያስን ያመኑት ወይ በእንግሊዝ እንደሚባለው ቦርቀቅ ያለ “ ቤኔፌት ኦፍ ዘ ዳውት” እንደሰጡት መገንዘብ እንችላለን--ግን ለምን ሆነ ለሚለው በበኩሌ መልስ የለኝም:: ይህ ሌላ ስህተት ነው:: ነገ ምን እርምጃ እንውሰድ ስንል የትላንቱን የዋህነትና ስህተት ለመድገም መነሳት የለብንምና ነው:: ከሻዕቢያ ጋር መገናኘ ት የለብንም የሚሉት ይህ አቅዋማቸው ድርጅትን በመገምገም ብቻ የታቀበ ከሆነ ብዙ ላይጎዳ ይችላል ግን ሕዝብን ከጠቀለለ ደግሞ ጉዳቱ ብዙ ነው:: ምክንያቱም የኢትዮጵያና ኤርትራ ሕዝብ አብሮ መኖሩ አስፈላጊ ከመሆኑ ሌላ አብረው መኖር ካልቻሉ በጋራ የሚጎዱ በመሆናቸው ነው:: ያለፈው አለፈ ብሎ ማለፍ ቢከብድም ነገን በሰላም ለዕድገት እንኑር ካልን ግን በሰላም የመኖሪያ መንገድ ማግኘት አስፈላጊ ነው:: በጉልበት ወያኔን ካስወገድን በኋላ በሀይል አሰብንም ወይም ጠቅላላ ኤርትራን እናስከብራለን ማለቱ በላውና ሊኖር በሚችለው ሁኔታ የሚያዋጣና የሚጠቅም ባለመሆኑም ነው::

5. ስለዚህም አፄ ኃይለሥላሴ እስራዔልን በተመለከተ ለግብፁ መሪ ለጋማል አብድል ናሰር ሲመክሩ “ ያለን ነገር የለም ማለት አይቻልም” ብለውት ነበር እንደሚባለው ኤርትራ ከኢትዮጵያ ተለይታ ራሷን የቻለች ሀገር መሆኗን መካድ አይቻልም:: በሀገር ደረጃ ይህን እውነታ አልቀበልም ማለት ህጋዊ መከላከያ ሆኖ ሊያገለግል ቢችልም በፖለቲካው መስክ ግን ዛሬን ለማስተዳደርና ለመጠቀም ስንነሳ ደግሞ የማይናቅ እንቅፋት ነው:: ይህ በዚህ ይቆይና ባለው ተጨባጭ ሁኔታ ምን ማድረግ ይገባል ለሚለው ምላሽ ለመስጠት ስንጥር በመጀመሪያ ሁኔታውንም መገንዘብ ያስፈልገናል::

ሀ / የመለስ ቡድን በሰላም ከሥልጣን የሚወገድ አይደለም፤

ለ / የመለስ ቡድን በትጥቅ ትግልና የከተሞች አመፅ መወገድ አለበት፤( ሁለገብ የሚለው ከወያኔ መደራደርንም ይጠቀልላል መባል ስለጀመረ ትቼዋለሁ)--

ሐ / የሕዝብ ጎራ የራሱ ጦርና ሀይል ሊያቋቁም ከቻለ የወያኔ ጦር አባል የሆኑትም ከድተው እየተቀላቀሉ ሊያጠናክሩት ይችላሉ፤

መ / ከሀገር ውስጥ በመነሳት ጦር ማቆም ቢቻልም ባለው ሁኔታ ከባድ ነውና የውጭ ወይም የጎረቤት እርዳታና ደጀንነትያስፈልጋል፤

ሰ / ኢትዮጵያን የከበቧት ሀገሮች ከሞላ ጎደል ለሕዝባች ትግል ቀና የሚያስቡ ና የሚበጁ አይደሉም፤
ረ / ፀረ ወያኔ ትግልን ለመርዳት አንዱ አማራጭ ወይም ደጀን ሊሆነን የሚችል ኤርትራ ነው::

በየነጥቡ አከራካሪ ጉዳዮችን ማንሳት መቻሉ እንዳለ ሆኖ ግን በኤርትራ መጠቀም ከተቻለ ለምን አንጠቀምበትም የሚለው ጥያቄ እንዲሁ የሚታለፍ አይደለም:: በኤርትራ መጠቀም እንችላላን ወይስ ሻዕቢያ ይጠቀምብናል? ይጫወትብናል ወይስ መቆጣጠር እንችላላን? ለዚህ የሚሰጠው መልስ ቁልፍ ወይም ወሳኝ ነው:: ኢሳያስ ወዳጃችን ነው ብሎ የሀገርን ዕጣ ባዕድ ነኝ ላለ ሰው አሳልፎ መስጠትን የሚያስቡ መቸም ቅጥረኞች ብቻ ናቸውና ነው::

6. አዲስ መልስ ለመስጠት ከመቃጣታችን በፊት ያለፈውን ያለውን እንመርምር:: የተወሰኑ ድርጅቶች ኤርትራ ሄደው ወይም በዚያው እየተረዱ ጦር መመስረታቸውን ነግረውናል:: አንጋፋው ኦነግ፤ የኦጋዴኑ ነፃ አውጪ ግንባር፤ የትግራይ ዴሞክራሲያው እንቅስቃሴ/ዴምህት/፤ የኢትዮጵያ አርበኞች ግንባር (ቀደም ሲል ይህ ግንባርና የጋምቤላው የቱሀት ፖል ቡድን ተዋህደው ነበር--ቱሀት ፖልም ከወያኔም ለመታረቅ ሲለማመጥ መክረሙን ደቡብ ሱዳኖቹ በቅርቡ አጋልጠዋል) በዚሁ በኤርትራ አሉ:: ከተሰነይ ወጣ ብሎ ባለ ቦታ የጦር ሰፈሮች አሏቸው ሲባል የመለስ ሰላዮች ሰርገው ገብተው የዴምህትን መሪ መግደላቸውም ተዘግቧል:: ለነዚህ ቡድኖች ሻዕቢያ በየጊዜው ወታደር አሰልጥኗል፤ መሳሪያ ረድቷል፤ተባብሯል:: ግራ ቀኙ፤ዘፋኙ የቀድሞ ደርጉ፤ አስመሳይ ፖለቲከኛው ወሬኛው ሁሉ ወደዚህ እየሄደ ታጣቂዎችን አገኘሁ ጎበኘሁ ማለት ብቻ ሳይሆን ተወካይ ነኝ ብለውም ሲነግሩን አድምጠናል:: ሻዕቢያ ረዳ፤ መገበ አስታጠቀ ተብሎ እንደሚወራው ሁሉ በአንፃሩ የደርጅቶቹ ጉዳይ ውስጥ ሻዕቢያ ጣልቃ ገብቷል፤ እገሌን አስሯል፤ ደብድቦ ገሏል፤ ለዚህ ወይ ለዚያ ድርጅት አዳልቷል፤ አሁንም ቢሆን የብሄረሰብ ቡድኖችን ይገፋፋል ይደግፋል ወዘተ የሚሉ ክሶችም መኖራቸውን መካድ አይቻልም:: ከሻዕቢያ ጋር ትብብር የሚሉት ክፍሎች በአሁኑ ወቅት ከፅሁፋቸው የሚገኘው ግምት በሀገሩ አንተ የሚባለው አቶ ኢሳያስና ድርጅቱን በተመለከተ ያላቸው ግንዛቤ ሚዛናዊና የሰከነ ሳይሆን ወደ ምራኀ አድናቆትና አመኔታ ያዘነበለ መሆኑ ነው:: እንገምግም ብሎ ለሚነሳ ነፃ ዜጋ ግን አቢይ ጥያቄዎች የመልስ ያለህ ብለው ይጮኻሉ::

ሀ / ሻዕቢያ እውን የአርበኞች ግንባርን ማጠናከርና ማሰማራት ካቀደ ወልቃይትና ኤርትራ ኩታ ገጠም መሆናቸው ያለ ነውና ለምን ብዙ ሺ ጦር አሰልጥኖ በማሰማራት ፈንታ 200-300 ታጋዮች ብቻ አሰልጥኖ የተወሰነ ትጥቅና ጥይት አስይዞ ሩቅ አርማጮሆና ቋራ ይሰዳቸዋል? በዚያ ወያኔ በተከታታይ ጦርነት ሲወጥራቸወና ጥይ.ታቸው ሲያልቅ ማን ጥይት መሳሪያ ይሰጣቸዋል? በሻዕቢያ ድብድባ ደርሶበት ሕይወቱ ጠፋ የተባለው ተስፋዬ ጌታቸው ይህን መቃወሙ ለሞት አልዳረገውም? ሻዕቢያ የአርበኞችን ግንባር ማጠናከር እየቻለ ለምን አልፈቀደም? ከሻዕቢያ

እናብር ባዮች ይህን ጥያቄ ማንሳት አለመፈለግ ብቻ ሳይሆን የመናፍቅ ጥያቄ ብለው ሊያወግዙ ትም መነሳታቸው የታየ ነው:: ዛሬም ቢሆን ሻዕቢያ ስሌቱ ማን አማራ ማን ሌላ የሚል ላለመሆኑ ከዚህ በላይ ምን መረጃ አለ ?

ለ / ሻዕቢያ በየጊዜው ግራ ቀኙን ኢትዮጵያዊ የተባለ ድርጅት፤ ቡድንና ግለሰብ ያስተናግዳል:: ይህ እውን ገንቢ ነው ወይስ ከፋፍለህ ተቆጣጠር ዘይቤ? ኤ ኤፈ. ዲ ሲመሰረት የሻዕቢያ ሚና አሉታዊ መሆኑ ታይቷል:: የኦነግን የባላይነት አስፍኖ እነ ሻለቃ ዮሴፍን ሊጋልቡ ያቀዱት ከሽፈ ል-- ግና ዕቅዳቸው ግን ተጋልጧል:: ለኢትዮጵያ ሳይሆን ሀገሪቷን ዳግም በብሄረሰብ መስነጣጠቅ መሆኑ በዚሁ ታውቋል:: ሀሎ ሻለቃ ዳዊት? ሀሎ ኤልያስ ክፍሌ? ይህን አታውቁም? ተኝታችሁ ነበር? ወይስ እናንተን በክብር የሚቀበላችሁ ሻዕቢያ ሌላውን በእስር ቤት ገርፎ ሊገድል መቻሉን ማወቅ አትፈልጉም? ይህም እስቲ ወደጎን ይቆይ:: ሻዕቢያ ኦነግንስ ቢሆን አጠናክሮ ለሥልጣን ሊያበቃው ከልቡ ሞክሯል? እባብን ያየ በልጥ ይበረግግ ነውና ሻዕቢያም ልጁ ወገኔ ያለው ወያኔ ከከዳው በኋላ ማንንም ሊያምን አልቻለም::

ሐ / በመሆኑም አርበኞች ግንባር ተባለ ኢሕአፓ፤ መአሕድ ተባለ ሌላ ለሻዕቢያ ሁሉም ቢፍቁት አማራ ነውና እሱን እንኳን ቢቀርቡት ( ስለ መአሕድና ኢሕአፓ መረጃ ባይኖረኝም) ከልቡ የሚ ተባበራቸው አልሆነም:: ቢሆንማ ኖሮ እዚህ ግቡ የማይባሉ ቡድኖችን ከማቀፍ እነ ቅንጅትን፤ ኢሕአፓን ወዘተ በቀና መንፈስ ለመቅረብና ትብብርን ለመመስረት በጣረ ነበር::ኤ ኤፍ ዲን ወይም ትብብር ለነፃነትና ለዴሞክራሲን በኦነግ ስር ሊያደርግ በመሞከር የትብብርን ሂደት ባላከ ሸፈ ነበር::

7. ሻለቃ ዳዊትና ሌሎቹም ኤርትራን የለም ከማለት አለ ብሎ በገንቢ መንገድ ለመያዝ መሞከር የሚሉት የአንጃው አዛውንት ከለፈፉት የተሻለና የሰከነ አማራጭ መሆኑ ቢታይም ከሻዕቢያ ጋር ዝምድና እባብን በኪስ መሆኑ መዘንጋት የለበትም:: ይህን ማለት ሻዕቢያን ዲያብሎስ ለማድረግ ሳይሆን እንደ ኤርትራ መንግሥት የራሱ ብሔራዊ ጥቅም አለውና የኢትዮጵያን ያስቀድም ያከብር ዘንድ አትጠብቁ ለማለት ነው:: ማለትም የራሳቸውን ጥቅም ለመጠበቅ የሚወ ስዱትን እርምጃ አንደምታ በማወቅ ተገቢውን የመከላከያ እርምጃ ለመውሰድ መዘጋጀት ያስፈል ጋል ማለት ነው:: ከሞኝ ደጃፍ ሞፈር ይቆረጣል ይሉን ድረስ መጃጃል አይገባንም ማለት ነው:: ሻዕቢያ እስካሁን እያሳየው ባለው አቅዋምና ድርጊት የኢትዮጵያን ሀልውና አክብሮ አዲስ የዝምድና መሰረት መፈለግን አላስቀደመም:: ኢሕአፓ አንጃ የሚለው ቡድን መሪ መሪ የከሰሱት እውነት ሆኖ ሻዕቢያ ከኢሕአፓ ጋር በቅርብ እየተመካከረ በመስራት ላይ ነው ቢባል ጆሮዬን ቀና ባደረግኩ ነበር-- ግን ይህ ሀሰት ነው:: ኢሳያስ የብሄረሰብ ድርጅት ጊዜያዊ ናቸው ቢልም ዘላቂ እንዲሆኑ አቅፎ እየደገፈ ነው:: ተቃዋሚ ነን የሚሉትም የፖለቲካ ድንግል ሆነውና ስለ ሻዕቢያ ምንም ጥልቅ ዕውቀትና ግንዛቤ ሳይኖራቸው ቲኬት እየቆረጡ አስመራ በመጓዝ ለሀገራቸው ሳይ

ሆን ለሻዕቢያ መሳሪያ እየሆኑ መሆናቸው እየታየ ነው፡፡ ይህም ሻዕቢያን ብልጥ- ጮሌ የእኛዎቹ ን ደግሞ--ይቅርታ--ጅል አላዋቂ-- ያደርጋቸዋል፡፡ የሻለቃ ዳዊት ፅሁፍ አዎንታዊ ሆኖ ሳለ ይህ ን መጃጃልና የዋህነት  አራጋቢ ሆኖ ታይቶኛል፡፡ በመሰረቱ ማለትም ከኤርትራ ሕዝብ ጋር አብሮ ለመኖር መጣር የሚለውን ብደግፍም ስለ ሻዕቢያ ያላቸውን ሀቅ አልባ ግምገማ አልጋራም ፡፡ ሻዕቢያም ሆነ ኢሳያስ መሰረታዊ የአመለካካት ለውጥ ለማድረጋቸው አሳማኝ መረጃ የለኝም፡፡ አቶ ኢሳያስንም እንደ ሌሎች አግኝቼ ባለማነጋገሬ የሰውየው ዲሰኩር በቅርቡ ለያደናግረኝ አል ቻለም፡፡ የሀገራችን ተቃዋሚ ሀይሎች ወደ አስመራ በየግላቸው ከመሮጥ በቅድሚያ እርስ በርሰ ተማካክረው የጋራ እርምጃ ቢወስዱ ይሻላል፡፡ ለሻዕቢያ ከፋፍለህ ተጫወትባቸውም ሰለባ እንዳይ ሆኑ፡፡ ፖለቲካ ፖለቲካ ነው--ሁሉም የራሱ ብሔራዊ ጥቅም ይቀድምበታል፡፡ እኛም ኢሳያስ ለኢትዮጵያ ደህንነትና ህልውና ሲል እንቅልፍ ያጣልን ትተን ምን መጠቀም እንችላለን ብለን መንቀሳቀስ አለብን ማለት ነው፡፡ ጥቅም ለሁለቱም ወግን መሆን አለበትምና ለእኛም ለነሱም የሚጠቅመውን ማወቁና መጠቆሙ ተገቢ ይሆናል፡፡ ኢሳያስን አምነዋለሁ ማለቱ ፖለቲካ ብሰለትን ሳይሆን ድክመትን ጠቋሚ ነው፡፡ እምነት በራስ ሕዝብ ላይ ብቻ ነው፡፡ የቀረቡት ፅሁፎ ች በብዛት ይህን መሰረታዊ ሀቅ የዘነጉ ይመስለኛል፡፡ ለዚህም ነው ከሻዕቢያ መጠጋቱ ለኢሳያስ ሳይሆን ለኢትዮጵያ ሕዝብ ትግል በእርግጥ ጠቃሚ ነውን ብለን ማወቅ ያለብን፡፡ ካልሆነ ግን ኢሳያስን አውቀዋለሁ፣ ጥሩ ሰው ነው፣ በቃሉ ይፀናል ወዘተ ልፈፋ ያሳለፍነውን የመከራ ዓመታ ትና ወያኔ እንዴት ለስልጣን እንደበቃ ሀቁን ላልረሳው ሕዝባችን መቸም ቢሆን አሳማኝ ሊሆን የማይችለው፡፡ ለነገሩ ይህ ዓይነቱ ውይይት ከወያኔ በሰ.ተጀርባ ቢካሄድ በተሻለ ነበር-- ግና መቸሰ ማል ጎደኒ ሆነ ሁሉም ነገር!

ወይይቱ በአመቺው መድረክ ይቀጥል.....